# የፍቅር ኪሣራ የጠብ ትርፍ የለውም!

*የወቅቱ የትግል ሥልት ‹በቃ፤ በአሰቃቂ የመንግሥት ሥርዓቶች መገፋት መንገላታቱ - መሰደድ መሰቃየቱ - መገደል መታሠሩ - መራብ መጠማቱ - መከፋፈል መለያየቱ በኛ ይብቃ፤ቢያንስ ከአሁን ወዲያ ያለው ትውልድ ይዳን› ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይና ሁልአቀፍ ዓላማ ውጭ ሌላ ግልጽም ይሁን ሥውር አጀንዳ የሚያራምድ አንድም የለዬለት ወያኔ ነው፤ አለዚያም በንሲዮ በገቢር ከወያኔ ጋር አንድ አምሳል ሆኖ የኢትዮጵያን ዳግም ትንሣኤ ለማደናቀፍ የሚማስን ጸረ ኢትዮጵያ ነው፡፡ እኔም «በዚህ የማይስማማ ‹ቡዳ ነው!›» እላለሁ፡፡ ቆምጨአምባው ታውሶኝ ነው፡፡ ሕዝቡ ለመሠረተ ትምህርት ሳይመጣለት ሲቀር ‹መሠረተ ትምህርት የማይመጣ ቡዳ ነው› ብሎ ለየት ያለች ባህላዊ ዘዴ በመጠቀም ዓላማውን አሳክቶኣል አሉ፡፡ ጥሩ አደረገ - ዋናው የልቡን መሙላቱ አይደል?*

*ታላቁ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ‹እርስ በርሱዋ የተከፋፈለች ቤት አትጸናም› ይላል፡፡ ይህ ወንጌላዊ ብሂል በማንኛውም ዘመን በየትኛውም ሥፍራ ለሚኖር የዓለም ሕዝብ ትልቅ አስተምህሮ የሚሰጥ ነው፡፡ ግን የሚያሳዝነው ነገር የሰው ልጆች ዋና ጠላት የሆነውና በጨለማ የሚመሰለው አፍራሽ ግብረ ኃይል* (Negative Energy) *አሁን ባለው የዓለማችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መድረክ ላይ ከምን ጊዜውም በበለጠ የጎላ ሚና እየተጫወተ በመሆኑ በተለይ ካለፉት ጥቂት አሥርት ዓመትት ወዲህ እጅግ በከፋ መልኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዜጎች ዘንድ መግባባትና መፈቃቀር እንዳይኖር እያደረገ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ሊያመልጡት ያልተቻለ ክፉ ማኅበረሰባዊ ዕጣ ለመረዳት የዓለምን ወቅታዊ ቅርጽ ማጤኑ ብቻ ይበቃል፡፡ አሁን ምድር ላይ የምናየው ትርምስና ውጥንቅጡ የወጣበት ሁኔታ በገሃድ የሚመሠክረው የብርሃን ኃይልን* (Positive Energy) *የበላይነት ሳይሆን የአፍራሽ ኃይልን የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመጨረሻ ፍልሚያ ነው፡፡ የዚህ አጥፊ ኃይል ምድራዊ የጎልውና ዘመን ማክተሚያ የደረሰ ለመሆኑ አንዳንድ ሃይማኖታዊና ኢሃይማኖታዊ ትንቢቶችና ጥልቅ ንጽጽራዊ የምርምር ውጤቶች እየገለጹ ይገኛሉ - ሰሚ አላገኙም እንጂ፡፡ ኢሃይማኖታዊ ያልኩት ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ለማለት እንጂ ‹ጸረ ሃማኖታዊ› ለማለት እንዳልሆነ ልብ ይባልልኝ፡፡*

*እኛ ኢትዮጵያውያንም የዓለም አካል በመሆናችን ለዓለም የታዘዘው በረከትም ይሁን መቅሰፍት በቀጥታ ይመለከተናል፡፡ ስለሆነም በነሊቢያ የደረሰው ሕዝባዊ አመጽ ወደኛዋ ሀገር አይዘልቅም ወይም በቻይናና በሃይቲ የደረሰው የመሬት መናወጥ በኢትዮጵያ አይከሰትም ማለት የዋህነት ብቻ ሳይሆን የዓለምን ውጫዊ የፖለቲካና ማኅበራዊ የለውጥ ሂደት እንዲሁም የመሬትን ውስጣዊ የተፈጥሮ እንቅስቃሴ ካለመረዳት የሚመነጭ ሞኝነትም ነው፡፡ እርግጥ ነው ‹ሰባት ዓመት የታወረ ነገ ዐይንህ ይበራልሃል› ቢሉት ‹የዛሬን እንዴት አድሬ!› አለ እንደሚባለው የዚያ ዓይነቱ በተለይም ብዙዎቻችን በጉጉት የምንጠብቀው የነጻነት ቀን መንቀራፈፍ ተስፋ የሚያስቆርጠንና ለዘመናት ካሳለፍናቸው መሪር የጭቆና አገዛዞች አንጻር አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሄድበት የነጻነት ቀን በደቂቃዎች መዘግየት ራሱ በዓመታት ያህል የዘገዬብን የሚመስለን ሞልተናል፡፡ ቢሆንም ቢያንስ ከ*42 *ዓመታት የአፍዝ አደንግዝ የጋዳፊ ሥራየ ቤታዊ አገዛዝ በሁዋላ በልዩ ቁጭት ከባርነት ለመውጣት ከተነሱት ሊቢያውያን ከፍተኛ ግንዛቤ ልንቀስም ይገባል፡፡ ያን የሊቢያውያንን ተቃውሞና እየተቀጣጠለ የመጣውን የ‹አንገዛም በቃን!› አመጽ የጠበቀ አልነበረምና፡፡ መለስ ዜናዊ በሕይወቱ ደንግጦ የሚያውቅ ከሆነ ሊቢያውያን ማመጽ ሲጀምሩ የደነገጠው ከሁሉም ድንጋጤዎቹ ታላቁ መሆን አለበት፡፡ ይህ ክስተት ለርሱም ትልቅ ዱብዕዳና የሚያስተላልፈው መልእክትም እጅግ አስደንጋጭ እንደሚሆንበት መጠራጠር የለብንም፡፡ ሌላው ቀርቶ በነዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ የሳዑዲ አረቢያ ሕዝብ እንኳዋን እልም ካለ የዘመናት እንቅልፍ በነግብጽና ሊቢያ ሣተና የነጻነት ጀግኖች ተቀስቅሶ በተቃውሞ ሰልፍ መብቱን እዬጠየቀ ነው፡፡ የ*36 *ቢሊዮን ዶላሩ የበጀት ጭማሪና የኢኮኖሚ ድጋፉ ማባበያ ከዚህ ከተነቃቃ የመብት ጥያቄው ሊመልሰው አልቻለም፡፡ ነገሩ የሎሚ ተራ ተራ ዓይነት ይመስላል፤*

ያለጥርጥር ነውም፡፡ ከዚህ በሁዋላ ያለው ጊዜ ለአምባገነኖች የማጥና የአዘቅት ሲሆን በተቃራኒው ለጭቁን የዓለም ሕዝቦች ደግሞ የነጻነትና የእፎይታ ነው፡፡ ይህ የአሁኑ የዓለም ገጽታ የማሟሟቂያ እንጂ ዋናው ማዕበል ገና መች ተነካና አልተጀመረምም የሚሉ ምሁራን አሉ፤ በተስፋ መጠበቅ ነው እንግዲህ፡፡ ለነገሩ እውነት ነው፤ ሊነጋጋ ሲል መጨለሙ ጥንትም የነበረ ነውና በአሁኑ ወቅት በዓለም የሚታየው ድቅድቅ ጨለማ የጠራ ንጋትን እንደሚያስከትል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

እንደ እግር እሳት ወደሚፈጀን የሀገራችን ጉዳይ እንግባና በተለይ ለውጥ ፈላጊዎች ነን በምንለው ወገኖች መካከል ስላለው አላስፈላጊ የመለያየትና ፊት የመነሳሳት አባዜ ግልጽነት ባለው ሠልጠን ያለ ሁኔታ ጥቂት እንነጋገር፡፡ ተብሎ ተብሎ ያለቀ አንድ እውነት እንካችሁ፤ የወያኔ ዕድሜ እንዲህ አለቅጥ የተንዘላዘለው በሱው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን በኛው የመከፋፈልና የመለያየት እስካሁንም ድረስ መድሐኒት ልናገኝለት ባልተቻለን ከፍተኛ ማኅበራዊ ነቀርሳ ምክንያት ነው፡፡ በጣም የምናሳዝን ሕዝብ ነን፡፡ የምናሳዝነው ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት እንታገላለን ብለን በመረጥነው የትግል ሥልት የወያኔን ሥርዓት ለመጣል በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የተሰለፍነው እንጂ ለማያባራ የመከራ ኑሮ ተዳርጎ ሕይወቱን በእዬዬ የሚገፋው ተራው ሕዝብ አይደለም፡፡ እሱማ አንድም ከፈጣሪው አንድም ከኛ ነጻነትህን በትግላችን እንዋጅሃለን ብለን ከምንታገልለት ነገር ግን ብዙዎቻችን እኛው ራሳችን ከገባንበት ጸረ ነጻነት የሆነ የጥላቻና የመገፈታተር አዙሪት የሚያወጣ ሌላ ነጻ አውጪ ከሚያስፈልገን አመኔታውን ከበላን ወገኖቹ አንዳች ነገር ይጠብቃል እንጂ ምን የተረፈ አቅም አለውና ወያኔን የመሰለ ወንበዴና ዘራፊ ቡድን ይታገላል? - የአንዳርጋቸው ጸጌን አባባል የኮረጅኩ አስመሰለብኝ መሰለኝ፡፡ ይሁን ግዴለም፤ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ቋንቋቸው ከቃላት አጠቃቀም ጀምሮ እንደሚመሳሰል ግልጽ ነው፡፡ እናም ተመሳሳይ ዓላማ አለን በሚሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል መነሻው በውል ተለይቶ የማይታወቀው ይህ ዓይነቱ መነቋቆርና ዓይንህን ላፈር መባባል በሚስተዋልበት ሁኔታ ሕዝብን ወደነጻነት አደባባይ ማውጣት ከባድ ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ የማይቻልም መሆኑን ያሳለፍናቸው የሃያ ዓመታት ተሞክሮዎች በሚገባ አረጋግጠውልናል፡፡ ተለያይቶ መጓዝ ለመጠፋፋት ካልሆነ ለሌላ ለምን ሊውል ዱሮስ? ደግሞም ክፋቱ ባለፈው የማይቆጨን መብዛታችን!

አሁን አሁን በአንዳንዶቻችን ጭንቅላት ውስጥ ያለው አንጎል የምንለው ነጭ ነገር በርግጥም የሰው ይሁን የዝንጀሮና የጦጣ መለየት የተቸገርንበት ወቅት ላይ የደረስን ይመስለኛል፡፡ ይገርማችሁዋል፤ እዚህ ሀገር ቤት ውስጥ ሕዝቡ አፉን በወያኔያዊ አፈማዝ ተለጉሞ፣ የኑሮ ውድነቱ ከማይመለከታቸው የሙስና ተዋንያንና የከፍተኛ ደመወዝ ተከፋዮች በስተቀር አብዛኛው ሕዝብ በቀን አንዴ እንኳዋን መቅመስ እያቃተው እንደክርስቶስ ኤሎሄ በሚልበት ወቅት በማይረቡና ሚዛን በማይደፉ ምክንያቶች የአንዲት ሀገር ልጆች ሚና ለይተው ወያኔን ሊጥሉበት የሚችሉበትን ሁለንተናዊ ኃይል በከንቱ ሲያባክኑ ይታያሉ፡፡ ይህ በተመሳሳይ ጎራ ውስጥ የሚካሄድ ጦርነት ከፕሮጋንዳ ጀምሮ ‹ዕድሉ›ን ካገኙት በመሣሪያም ሳይተጋተጉ የሚቀሩ አይመስሉም፡፡ ይህ ሁሉ ከንቱነት ነው፡፡ የነጻነትን ትርጉምም አለመረዳት ነው፡፡ የሕዝብን ችግርም አለማወቅ ወይም ለማወቅም አለመፈለግ ነው፡፡ ለራስ ጠባብ የሥልጣንና የሀብት ፍላጎት አደግድጎ መቆምም ነው፡፡ የቆዬ ጥላቻን እያነገሉ ግላዊ ቂም በቀልን መወጣትም ነው፡፡ ከሕዝቡ ችግር ይልቅ ለራስ ፍላጎትና ለብቀላ ስሜት ቀዳሚውን ትኩረት በመስጠት በሕዝብ ቁስል እንጨት መማገድም ነው፡፡ በሕዝብ እየማሉና እየተገዘቱ በፖለቲካ ስም የራስን ፍላጎት ማራመድም ነው፡፡ ብዙና ብዙ ብሶት ወለድ ወቀሳዎችን መደርደር ይቻላል - አሁን አይጠቅሙም እንጂ፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ በእናታቸው ማህጸን ውሃ ሆነው ቢቀሩ የሚሻላቸው ማፈሪያ ዜጎች እውነቱን ሲነግሩዋቸው አይወዱም፤ እውነት ህቅ እንቅ ታደርጋቸዋለች፡፡ የተሠሩበት አጥንትና ጅማት ከእስስትና ከጅብ በመሆኑ ይመስላል ብዙዎቹ ትግል አሰናካይ ወገኖች መልካቸውን እንደጊዜው የፖለቲካ ንፋስ እዬቀያየሩ ሆዳቸውን በሚሞላ ለነሱ ብቻ

አንገብጋቢ በሆነ ጉዳይ ላይ ተጠምደው ነው የሚስተዋሉት፡፡ እውነቱ ሲነገራቸው ግን የዋሃንን እያስተባበሩ ወይም መሰል ሆዳሞችን ከየሥፍራው በጥቅም እየማረኩ ከነሱው ጋር በማሠለፍ እውነቱን በሚነግሩዋቸው ላይ የተቀነባበረ የስም ማጥፋትና ሌላም እነሱ ብቻ የሚያውቁት ዘመቻ ያካሂዳሉ፡፡ ሕዝቡ ግን ይታዘባል፤ ማንም የፈለገውን ቢሠራ ለጊዜው የወቅቱ ፖለቲካዊ ሽፋፋ ሚዛን እስከፈቀደለት ድረስ በሕዝብ ላይ አይሠሩ ግፍ እዬሠራና የሕዝቡን የሰቆቃ ኑሮ በማራዘሙ ረገድ የበኩሉን አሉታዊ ሚና እየተጫወተ የተወሰነ ጊዜ ሊቆይ ይችል ይሆናል እንጂ ከታሪክ ፍርድ ግን መቼም ቢሆን በፍጹም ሊያመልጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ የሚያዋጣው ብቸኛው መንገድ ... ቆይ ... ቆይ ሌላ ነገር ትዝ ብሎኛልና ወደዚያ ልሂድ በቅድሚያ፡፡

በድረ ገጾች አካባቢ የሚታየው ነገር ደግሞ በጣም ይገርማል፤ ክፉኛ ያሳዝናል፤ ያስደነግጣልም፡፡ የድረ ገጽ እናት በድባብ ትሂድ ለኢትዮጵያ ነጻነት ቆመናል የሚሉ በርካታ ድረ ገጾች በተለይ በምድረ አሜሪካ ሞልተዋል፡፡ እውነቱን ለመናገር አንዳንዶች ግን ድረ ገጻቸውን ዘግተው በሌላ ሙያ ቢሠማሩ ይሻላቸዋል - ለምሳሌ ድጋፍ በማሰባሰብና ሌሎች ድርጅታዊ ሥራዎችን በመሥራት ትግሉን ሊደግፉ ይችላሉ፡፡ የሚዲያ ሙያ የስሜት አምባላይ ፈረስ በውርድንብር እየጋለቡ እንደሳት ራት ዘልለው የሚሞጀሩበት አይደለም፡፡ ሚዲያ የራሱ ሙያዊ ሥነ ምግባር ያለው እንጂ በጃሎ መገን እንደፈለጉ የሚፏልሉበት እንዲሆንም አይጠበቅም፡፡ በሚዲያ ‹ሲሞቅ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ› እንደምንለው የጣመህን ብቻ የምታቀርብበት ላንተ ያልጣመህን ግን ወደ መሬት ጥለህ አፈር የምታስግጥበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ እየመረረህ የምታቀርባቸው እየጣፈጠህ ደግሞ ሳታቀርብ የምትተዋቸው ከሰው የተላኩ መልእክቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ላንተ ላንዱ ጋዜጠኛ ብቻ ስላልጣመህ ወይም ስለጣመህ የማታወጣና የምታወጣ ከሆነ በሙያው ውስጥ ያለህ ይመስልህ ይሆናል እንጂ የለህም፤ ወያኔዎች በጉልበት የያዙትን ሥልጣን እንደፈለጉ እንደሚፈነጩበት ዓይነት ይሆናል ከሙያዊ ሥነ ምግባር እየወጡ ሙያን ማራከስ፡፡ እርግጥ ነው በጉልበት የተያዘ ነገር ማንም ከልካይ ስለሌለ እንደተፈለገ ቢፈነጠዙበት ሌላ ጉልበተኛ እስኪመጣ ድረስ ይቻል ይናል፡፡ የሚዲያ ሥራ ግን በስሜትና በጉልበት እንዳሻ የሚኮንበት ሳይሆን በዕውቀትና በችሎታ እንዲሁም በአርቆ አሳቢነትና በመቻቻል ሊከናወን ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር የዓለም ሚዲያዎች ሲመዘኑ ስንቶቹ መሥፈርቱን እንደሚያሟሉ የዘርፉ ባለሙያዎች መጠነኛ የዳሰሳ ጥናት አድርገው ቢያሳውቁን የተሻለ ይሆናል፡፡

የኞቹን በሚመለከት ግን ከትዝብቴ ጥቂት ነገር ብቻ ብጠቁም የሆነ ሽክም የወረደልኝ ያህል ስለሚሰማኝ ትንሽ ልተንፍስ፡፡ ደግሞስ በስንቱ ታፍኜ እዘልቀዋለሁ? ለጊዜው ስም አላነሳም፡፡ ቅጽሎችን መጠቀም ግን መብቴ ነው፡፡

ብዙዎች ድረ ገጾች እኔንም ጨምሮ አብዛኞች ጫሪዎች የምንልከውን መጣጥፍ በክብር ተቀብለው **ጣማቸውም አልጣማቸውም** ያስተናግዳሉ - ከኤዲቶሪያል ፖሊሲያቸው እስካልተጋጨ ድረስ - ሊያውም ያም ያላቸው ብዙዎች ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ የምንልከው ነገር ከጣማቸው እሰዬው ፤ ካልጣማቸውም እሰዬው፡፡ ለምን ቢባል አንድ ነገር ለሁሉም እንዲጥም አይጠበቅበትምና ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮ ውጪም ነውና፡፡ ልዩነት ያለ ነው፤ የምንጽፈውም ልዩነት ስላለ እንጂ ልዩነት ባይኖርማ ማን ሌላ ሥራውን ትቶ ወረቀት ሲሞነጭር ይውላል? ልዩነትን ወደጥቅም መለወጥ ግን ከብልሆች የሚጠበቅ ነው፡፡ ችግር የሚፈጠረውና ዜጎችን ላልተፈለገ ግጭት የሚዳርገው ልዩነት በተፈጠረ ቁጥር፤ ‹አካኪ ዘራፍ! ይቺን ይወዳል የሰውዬው ልጅ!› በማለት በረባውም ባልረባውም እጅጌን መሰብሰብ የሚዘወተር ከሆነ ነው፡፡

አንዳንድ ድረ ገጾች ራሳቸው ነጻነት ያላቸው አይመስሉም፤ በሆነ ኃይል ጫና የሚደረግባቸው ወይም ከሆነ አቅጣጫ ቁጥጥር ያለባቸው ይመስላሉ፡፡ በዚያም ምክንያት ማለፊያ መጣጥፎች ከሰዎች ቢደርሳቸውም እንኩዋን እንደማያወጡ ምልክቶችን አያለሁ፡፡ እርግጥ ነው በገቢ ራሱን የማይችል የሚዲያ ማዕከል ድጋፍ ለሚያደርግለት አካል ቅን ታዛዥ እንደሚሆን

ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር ግን ከዓላማ ያዛንፋል፡፡ ለትክክለኛ ዓላማም አያቆምም፡፡ የአንባቢን መብትም እንደመጋፋት ሊቆጠር ይችላል፡፡ አንባቢ ሞግዚት አያስፈልገውም፡፡ በ‹እኔ አውቅልሃለሁ› ያረጀ ያፈጀ ዘይቤ ምናልባትም ለአንድ ቃል ወይም ሐረግ ከዐውድ ውጪ በሚሰጥ የግል ትርጉም የአንድን ሰው ጽሑፍ ከማዕድ ብናገልለው የሰውዬውን ልፋት ከቁብ አለመጣፋችን እንዳለ ሆኖ የአንባቢን የመረዳትና ሃሳብን የማንሸራሸር አቅም ማሳነስ ነው፡፡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ከሚያስፈልጋቸው በተለይ የሃይማኖትና የጎሣ ግጭቶችን ሊቀሰቅሱ ወይም ሊያባብሱ ከሚችሉ ጽሑፎች በስተቀር ሌሎችን ለአንባቢው የኅሊና ፍርድ መተውና በተቻለ መጠን አንዱ ለአንዱ መልስ እየሰጠ እንዲማማሩ ማድረግ የበለጠ ትምህርታዊና ገምቢ ይሆናል፡፡

አንዳንድ ድረ ገጾች ደም የተቃቡ ይመስል ጋዜጠኞቹ በአካል እንኳን ሳይተዋወቁ በመካከላቸው የሰገሌን ጦርነት ሲያካሂዱ መታዘብ ለምደነዋል፡፡ ሃይ ባይ ማጣታቸው እንጂ ይሄኔ የግጭታቸው መንስኤ በጣም ቀላል ይሆናል፡፡ ይህ ነገር ከአንድ ለሀገር ከቆመ የሕዝብ ሰው አይጠበቅምና ከአሁን ወዲያ እንዲቀር እለምናለሁ፤ እጸልያለሁም፡፡ አሁንም‹ እርስ በርስዋ የተለያየች መንግሥት አትጸናም› የሚለውን ቅዱስ ቃል ላስታውስ እፈልጋለሁ፡፡ ፍርዶችን ለፈጣሪና ለታሪክ ሰጥተን እኛ ሊያስማሙን በሚችሉ ቢያንስ በመለስተኛ ጉዳዮች ተስማምተን ትግላችንን እንቀጥል፡፡ ጣት መቀሳሰሩ ከንግዲህ ይቅርብን፡፡ በዚያ ላይ ዋና ፈራጅ ሕዝብ አለና እኛው ለኛ ከሳሽና ጠበቃ ሆነን በምናገለግለው ሕዝብ መሃል ለትዝብት የሚያጋልጠንን ነውር ድርጊት አንፈጽም፡፡ ጆሮ ያለው ይስማ!

አንዳንድ ድረ ገጾች የሚታገሉት ከማን ጋር እንደሆነ ራሱ የሚያውቁ አይመስሉም፡፡ እንደዶን ኪሾት ከንፋሱም ከተራራውም ከወንዙም ከገደሉም የሚጋጩ ይመስላሉ፡፡ አንድ ሰው አንድ ነገር ሊያደርግ ሲያስብና ሲያቅድ ዓላማውን ቁልጭ አድርጎ መንደፍና ያንኑንም ማራመድ ይገባዋል፡፡ ሥልታዊ መሆንም ኃይልና ጉልበት በከንቱ እንዳይባክን ያግዛል፡፡ ከፊት ለፊት ከተገኘው ሁሉ ጋር እንጋጭ ብንል የምንጋጨው ይበዛና በመጨረሻ ልንጋጨው ከፈለግነው የግጭታችን አንኳር ኃይል ጋር ሳንጋጭ የመጋጨቱ አምሮትም ሳይወጣልን ባጭር ልንቀጭ እንችላለን፡፡ ግሥላ የምትሞተው አዳኞችዋ በሚጠነስሱባት ተንኮል ነው ይባላል፡፡ ዛፍ ላይ ያለችዋን ግሥላ ያናድዱዋትና ጋሻቸውን አጥብቀው በመያዝ ጉድጓዳቸው ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ ግሥላዋ ሰውዬውን ያገኘች መስሎኣት ጋሻውንና አካባቢውን በንዴት እየተንጨረጨረች ትነክስና በመጨረሻም ማንም ሳይነካት በንዴት ትሞታለች፡፡ አዳኙም አቧራው መብረዱን ሲረዳ ከጉድጓዱ ወጥቶ ግዳዩን ለፈለገው ዓላማ ያውላል፡፡ በሆነ ባልሆነው እንደግሥላዋ እየተንጨረጨሩ ላገኙት ሁሉ የባላንጣነትን ታርጋ የሚለጥፉ የችግራቸው መንስኤ ምናልባትም ያለመብሰል ወይም ‹ከመጠን በላይ መብሰል› የሆነባቸው ዜጎቻችን ይህን የሚያናጫቸውንና ካገኙት ጋር የሚያላትማቸውን (ሥነ ልቦናዊ) ችግር በንባብና ረጋ ብሎ በመደማመጥ እንዲሁም በጸሎትና በአርምሞ ወደኅሊና በመመለስ ለመቅረፍ ቢችሉ ከሀገራችን በፊት እነሱ ራሳቸው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ አለበለዚያ የሌለን ጠላት እየፈጠሩና አጠገብ ያለን ወገን ካለምንም ተጨባጭ መረጃ ወደሩቅ ብዕሲነት በመለወጥ እንደጠላት እየፈረጁ፣ ከሁሉም ተጠርጣሪ ጋርም እየተላጉ የትም መድረስ አይቻልም፡፡ መተማመን ካለመተማመን የበለጠ ዋጋ እንዳለውም መገንዘብ አይከፋም፡፡ ብዙ ነገሮችን የምናደርገው እንዲሁ በማመንና በመተማመን ነው፡፡ ጧት ከቤታችን ስንወጣ በሰላም ውለን በሰላም ወደቤታችን እንደምንመለስ እምነት ጥለን እንወጣለን እንጂ ከማንም ጋር የ‹ደህና አውለኝ› ውል አንፈራረምም፡፡ ቡና ቤት ገብተን ምግብ አስቀርበን ስንበላ ወይም መጠጥ ቤት ገብተን ያሻንን መጠጥ አዝዘን ስንጠጣ እንዲሁ አምነን እንጂ አሁንም ከአሣላፊዎች ወይም ከሥራየ ቤት ሰዎች ጋር ለደኅንነታችን - በምግብና መጠጡ ላለመመረዛችን - የዋስትና ውል ተፈራርመን አይደለም፡፡ ስለዚህ እባካችን እርስ በርስ መጠራጠራችንንና መወጋገዛችንን ተጨባጭ ነገር በሌለበት ሁኔታም መወነጃጀላችንን ገደብ እናበጅለት፡፡ ከትናንት የተሻለ ስብዕና ባለቤቶች በመሆን የዛሬና የነገ ሕይወታችን ትርጉም ያለው እንዲሆን ለማድረግ

በጋራ እንጣር፡፡ ሁሉንም ተጠራጥረንና በጠላትነት ፈርጀን አንዘልቀውምና ቆም ብለን በማሰብ ወዳጆችን ስለምናበዛበት መንገድ እንምከር፡፡ በፍቅር ብዙ እናተርፋለን፤ በጠብ ግን ብዙ እንከስራለን፡፡ በተጨማሪም ጠብን የግል ፍቅርን የጋራ ማድረግ ይገባናል፡፡ ከነተረቱ ‹ የጠብ ደቦ የለውም› ይባላል፡፡ ለጠብና ለግጭት ፊት ባለመስጠት ለጋራ የአንድነታችን አውታሮች መጠናከር ቅድሚያ እንስጥ፡፡ ይህን ማድረግ ያለብን በፍቅር እንጂ በጠብ የትም መድረስ ስለማንችል ነው፡፡ ያለፈ ታሪካችን የሚያስተምረንም ይህንኑ ነው፡፡ እኛ በተጋጨን ቁጥር ጠላቶቻችን ጮቤ ይረግጣሉ፡፡ እኛ በተተለመልን ዘውጋዊም ይሁን ሃይማኖታዊ የግጭት ጎዳና በተመምን ቁጥር የጠላትን አጀንዳ እያስፈጸምን መሆናችንን አንዘንጋ፡፡ ለራሳችን እኛው ካላወቅን ማንም ሊውቅልንና ከገባንበት የችግሮችና የችጋሮች አረንቋ ሊያወጣን አይችልም፡፡

አልፎ አልፎ በአንዳንድ ድረ ገጾች ብቻ የማያቸው በጣም ግሩም ጽሑፎች በሌሎች ላይ ላያቸው ሳልታደል እቀራለሁ፡፡ ድረ ገጾቹ ግን የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ንብረት ከመሆናቸውም በላይ የጸሐፊዎቹም ሆነ የአስተናጋጅ ጋዜጠኞቹ ዓላማ ያው ከከፋፋዩ ወያኔ ነጻ የሆነችና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሠፈነባት ኢትዮጵያ እውን ሆና ማየት ነው፡፡  በዚህ በትልቁ ዓላማ አንድ የሆኑ ወንድሞችና እህቶች በማላውቀውና በርግጠኝነትም ከሀገራዊው ታላቅ ዓላማ አኳያ አንዳችም ሚዛን በማያነሳ ጉዳይ ተቃቅረው ሲገፈታተሩ ማየት ቅስምን ይሰብራል፤ በተወሰነ ደረጃም ተስፋ ያስቆርጣል፡፡ ትግላችን ከዓላማ አንድነት ሳይሆን ከግለሰብ ጋር ከተያያዘ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት አለው፡፡ ግለሰብ አላፊ ጠፊ ነው፡፡ የሀገር ነጻነት ጉዳይ ግን ዘላቂና ማኅበረሰብኣዊም ነው፡፡ ስለዚህም የጠባቸው መንስኤ ምንም ይሁን ምን ነገር ግን በጣም ወቅታዊና አንገብጋቢ መልእክት የያዘ ጽሑፍ (ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች ያስቀመጥኩትን የመሰለ) በጥቃቅን ስሜት ወለድ ቁርሾዎች ወይም አለመግባባት ምክንያት ትኩረት ሲነፈገው ሳይ በበኩሌ እጅግ አዝናለሁ፡፡ ይህም ሁኔታ ባልዋን የጎዳች መስሏት በጋሬጣ ሰውነትዋን የቧጨረችውን ሞኛሞኝ ሚስት ያስታውሰኛል፡፡ የበቀለ ከአደፍርስ ወይም የሐጎስ ከፍትዊ አሊያም የደቻሳ ከሂርጳሳና የዘበርጋ ከኤርሱሎ መቀያየም ከሀገራዊ የነጻነት ትግል ጋር ለምን እንደምናገናኝ አይገባኝም፡፡ ይህ ዓይነቱ የልጆች ዓይነት ባሕርይም ትዝብት ውስጥ ያስገባናል፡፡ እናም ‹**መቼ ነው በጥሞና በመነጋገር ሳንጣላ የተጣላንባቸው የሚመስሉ ልዩነቶቻችንን የምናስወግደው?**› ብዬ ራሴን ስጠይቅ የመልሱ ማጠጥ ራሴን ያሳምመኛል፤ ፡፡  የአንዲት እናት ልጆች መሆናችንን በጭራሽ ዘንግተን አንዳችን ሌላኛችንን እንደባእድ በመቁጠር በከንቱ የምንቆራቆሰው እስከመቼ ነው? ይህ ዓይነቱ መጥፎ ጠባያችንስ አይደለም ወይ የወያኔ ባሪያዎች አድርጎ ኮድኩዶ ይዞን ያለ? መቼ ነው ከተዘረጋልን ወጥመድ ወጥተን የራሳችን ጤናማ ስብዕና ባለቤቶች የምንሆነው? ኅበዝ ብዙ ችግሮች አሉብን፡፡ እነዚያን ችግሮች ሸፋፍነን የጋራ መፍትሔ ለመሻት መባዘኑ በቀላል የጨዋ አገላለጽ አያዋጣንም ባይ ነኝ፡፡

«ጮሃ የማታውቅ ወፍ ስትጮህ ‹እለቁ እለቁ‹ ትላለች» እንደሚባለው እንዳይሆንብኝ እንጂ ዛሬ በውስጤ የሚያብሰከስከኝን ነው ዘርግፌ የነገርኳችሁ፡፡ የሚያወጣ ያውጣው ፤ የማያወጣም ይተወው - ለምጀዋለሁ፤ እውነቱ ግን ይሄው ነው፡፡ ዋጮ ቢገለበጠ ያው ዋጮ ነው ይባላል፡፡ እውነትንም ሸፈንናት ወይ ቀበርናት ያው ናት፤ አትሞትም፤ አታረጂም፤ ቀጥናም ተበሳቁላም ገሃድ የመውጫ ጊዜዋን ትጠብቃለች፡፡ እኔ ግን ተወረድኩት፡፡ መጽሐፉም ‹ሂዱና ንገሩዋቸው ከተቀበሉዋችሁ ጥሩ፤ ካልተቀበሉዋችሁ ዕዳው የነሱ እንጂ የእናንተ አይደለም፤ ነገር ግን የዕዳው ተካፋይ እንዳትሆኑ የእግራችሁን አቧራ ሳይቀር አራግፋችሁ ከዚያ ሥፍራ ውጡ› ይላል፡፡ የማን መጽሐፍ? አታስዋሹኝ አሁን ተዘንግቶኛል፡፡

ወደሚያወጣን ብቸኛ መንገድ እንመለስና ነገሬን ልቋጭ፡፡ የሚያወጣን ብቸኛው መንገድ የወያኔን ሥልት መኮረጅ ነው፡፡ ወያኔ ሀገርን ለማጥፋት ከኢትዮጵያ ታሪካዊና ስትራቴጂያዊ ጠላቶች ጋር ትብብርን መፍጠሩ የሚታወቅ ነው፡፡ አንድን የጋራ ጠላት ለማሸነፍ እንኳንስ ተነጣጥለውና ተጎሻምጠው ተባብረውም አንዳንዴ ያስቸግራል፡፡ በዚህ በያዝነው የመኮራረፍና የመናናቅ፣ አንዱ አንዱን የማበሻቀጥና የማጥላላት፣ አንዱ በጎሣና በጎጥ በመደራጀትና ሌላው

በሃይማኖትና በመንደር ልጅነት በመሰባሰብ … በሚደረግ የተናጠል ትግልና የተከፋፈል ኃይል ሀገር ነጻ ትወጣለች ብሎ ማሰብ ቂልነትና ላም አለኝ በሰማይ ዓይነት ነው፡፡ ይህንን አካሄድ አይተነው አይተነው በቅቶናል፤ እንዲያውም ለዚህ ዓይነቱ የትግል ሥልት ሕዝቡ የሚሰጠው አንድም ሞራላዊም ይሁን ማቴሪያላዊ ድጋፍ የሚኖር አይመስለኝም፡፡ በዚያ ረገድ ሰልችቶናል፤ ደክሞናልም፡፤ እናም የሚያወጣው ብቸኛው መንገድ በጎሣና በነገድ ሳይከፋፈሉ በአንዲት ኢትዮጵያ ጥላ ሥር የጋራ ሀገር መፍጠር ብቻ ነው፡፡ ይሄ ያለፈን ነገር - የእውነትም ይሁን የፈጠራ -  ከተቀበረበት እየፈነቀሉ መወቃቀሱና መጎነታተሉም ወያኔዊ እንጂ ከጤናማ አእምሮ የሚፈልቅ ጠቃሚ አካሄድ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁሉም ከተባበረ ነጻነታችን ቅርብ ነው፡፡ እንደስካሁኑ ከተሄደ ወይዘሪት ነጻነት የውሃ ሽታ እንደሆነች ትቀራለች ማለት ሳይሆን የትግሉ ጊዜ አለቅጥ ይራዘማል፤፤ በውጤቱም የሕዝብ መከራና ሥቃይ በባሰ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ ጠላቶች የሚፈልጉትም ይህንን ነው፡፡

ትግሉ ከየት ይጀምር? ከድረ ገጾች፡፡ መቼ? አሁንና ዛሬውኑ፡፡ እንዴት? መኮራረፍ ይቁም፡፡ ልባችን ቂምንና ኩርፊያን ይሠርዝ፤ በምትኩ በመግባባትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ መዋደድና መፋቀር በሁሉም ዘንድ ይናኝ፡፡ ብዕሮቻችን ፍቅርንና መተሳሰብን ይስበኩ፡፡ በመፈቃቀር የምንከስረው አንድም ነገር እንደሌለ ራሳችንን እናሳምን፡፡ በመለያየታችን ግን ብዙ ነገር እንዳመለጠን እንረዳ፡፡ ከአሁን በሁዋላ በዜጎቻችን መካከል ጠብንና መከፋፈልን የሚያባብሱ ጽሑፎችን ሳይሆን ፍቅርንና አንድነትን የሚያበዙ፣ ወደ ነጻነት አደባባይ እንድንደርስ መንገድ የሚጠርጉ ከማንምና ከየትም የሚላኩ መጣጥፎችን ለማስተናገድ ቆርጠን እንነሳ፡፡ ጸሐፊዎቻችን የኛንም እገዛ እንደሚሹ ተገንዝበን በሚያጠፉ ጊዜ ከቀና መንፈስ በመነሳት ከቁጡ ቃላትና ከስሜታዊነትም በመራቅ ምክራችንን እንለግስላቸው፡፡ የሁላችን የጋራ ትኩረት ባንድ ላይ ተሸምኖ ለአንዲት ዴሞክራሲዊት ሀገር ግንባታ የሚውል ከሆነ አፍታ እንደማይፈጅብን እንወቅ፡፡ ለዚያ ሂደት ግን ሕይወት ሰጥቶ የመቀበል መድረክ ናትና ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል እንዘጋጅ፡፡ ጎጂ አቋምንና አመለካከትን ማስወገድና በምትኩ ገንቢና አቀራራቢ የሆነ አመለካከትና አቋምን መያዝ በዚያውም የዕርቅን መንገድ መከተል ጠቀሜታው እንደገና የመወለድ ያህል ነውና በኢትዮጵያ አምላክ ይሁንብን ከእንግዲህ ለከፋፋይ ሰይጣናዊ አስተሳሰቦች ተገዢ አንሁን፡፡ በመካከላችን ተሰግስገው የሚለያዩንን እኩይ ዜጎች እንንቃባቸውና ‹እዚያው በጠበላችሁ› እንበላቸው፡፡ እስካሁን ብዙ የተጎዳነው ራሳችን ለራሳችን ምቹ ስላልሆንን እንጂ በወያኔ ብቻ እንዳልሆነ ተረድተን ዛሬውኑ እንስተካከል፡፡ ካልተስተካከልን ለይቶልን ጠፋን ማለት ነው - ቢያንስ ቀጣዩ ትውልድ እንደባብ አፈር ልሶ ተነስቶ ራሱን ነጻ አእስኪያወጣ ድረስ፡፡ እግዚኣብሔር ኢትዮጵያንና የተገፋውን ሕዝቧን ይባርክ፤ እንደጨው ዘር በመላዋ ዓለም የተበተነውን ሕዝቡዋንም ይሰብስብ፡፡ ዳግመኛም የሀገር አውራ ያድርጋት፡፡ ምቀኛዋንና ጠላትዋን እንደቀድሞው ዘመን ከእግሩዋ ሥር አስገዝቶ የጥንቱን ግርማ ሞገስና ተፈሪነትዋን ይመልስላት፡፡ አሜን፡፡

Here is the gist of this letter, the real message from the grassroots: a nation outraged by high soaring inflation; a public scandalized by unprecedented corruption, rampant unemployment, political oppression, chronic shortage of land in rural areas. In sum, the nation is desperate for change.

You have essentially wasted the two decades with which you were blessed to affect change. In place of pragmatism dogma has prevailed; in place of transparency secrecy has taken root; in place of democracy oppression has intensified; and in place of merit patronage has been rewarded.

Ato Meles Zenawi: the people want -- no, need -- you to leave office.

The people are closely watching events in North Africa as I write this letter. They are debating the implications for Africa, including Ethiopia. And they have been inspired by the heroism of ordinary Libyans.

Listen to them before it’s too late.

**ከዚህ በላይ የተቀመጠው ከዕውቁ የሀገር ሀብት ከጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሰሞነኛ ጽሑፎች የተቀነጨበ ነው፡፡ ይህ ጽሑፍ ምን ይወጣለትና ነው መድረክ እንዲያጣ የሚደረገው? በእውነት ለሁላችንም የቤት ሥራ ይሁንነና አካሄዳችንን እንፈትሽ፡፡ ማስተካከል የሚገባን ነገር ካለ ጊዜ ሳንሰጥ እናስተካክል፤ እንደግለሰብ ለኛ ሳይሆን ለሀገራችን ስንል፡፡**

netsanetzegeye3@gmail.com